

# ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን መመገቡ

- ኢየሱስ ተአምራትንና ድንቆችን ያደር ስለነበር ብዙ ሰዎች ተከሉት። የተከተሉበት ምክንያትም ለራሳቸው፣ ለወዳጆቻቸው ወይንም ለዘመዶቻቸው ፈውስን ፍለጋ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ አገልግሎት ስለበዛበዘቸው ለመመገብ እንኳን ጊዜ አልነበራቸውም። ስለዚህ ኢየሱስ ለተወሰነ ጊዜ ማረፍ ይችሉ ዘንድ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ወደሌላ ቦታ ለመሄድ አሰበ። ይህ በዚህ ወቅት በጣም ከባድ ነገር ነበር። ምክንያቱም ኢየሱስ የመጥምቁ ዮሐንስን ሞት የሰማበት ጊዜ ስለነበር ነው።

- ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱም የገሊላን ባህር ብቻቸውን በጀልባ ተሻገሩ። ሆኖም ብዙ ሰዎች ወዴት እንደተጓዘ ስላወቁ በዙሪያ ከነበሩ ከተሞችና መንደሮች ሳይቀር በባህሩ በሌላኛው ዳርቻ በኩል ቀድመውት ጠበቁት። ኢየሱስ የተከተሉትን ሰዎች ሲመለከት አዘነላቸው። ያለእረኛ በሜዳ ላይ እንደተተዉ የበግ መንጋዎች ይመስሉ ነበር። ኢየሱስ ስለእግዚአብሔር መንግስት ካስተማራቸው በኋላ ሕሙማንን ደግሞ ፈወሳቸው።

- እየመሸ ስለነበርም ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን የተሰበሰበውን ሕዝብ እንዲያሰናብትና በአካባቢው ካሉ መንደሮች የሚበላ ምግብ ፈልገው ወይንም ገዝተው እንዲመጡ እንዲነግራቸው ጠየቁት። ሌሊቱንም በዚያ እንዲያሳልፉ እንዲያደርጋቸው አሳሰቡት። ኢየሱስ ግን “መሄድ አያስፈልጋቸውም፤ የሚመገቡትን እናንተ ስጧቸው።” አላቸው። ደቀመዛሙርቱ ለዚህ ሁሉ ሰው ምግብ ለመግዛት በቂ ገንዘብ እንደሌላቸው ያውቃሉ። በዚያ ስፍራ ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል አምስት ሺዎቹ ወንዶች ሲሆኑ ከእነርሱ በተጨማሪም ያልተቆጠሩ ብዙ ሴቶችና ሕፃናት አብረዋቸው ነበሩ።

- ኢየሱስም ፊሊጶስን እንጀራ ከየት መግዛት እንደሚችሉ ጠየቀው። ኢየሱስ ይህን የጠየቀው ሊፈትነው ነበር። እንዴት ይህን ሁሉ ሕዝብ መመገብ እንዳሰበ ያውቅ ነበር። ፊሊጶስም በዚያ ስፍራ የተሰበሰበውን ሕዝብ ጥቂት ጥቂት መመገብ ቢታሰብ እንኳን ወደ ሁለት መቶ ዲናር እንደሚያስፈልግ ለኢየሱስ ነገረው። ሁለት መቶ ዲናር ማለት በዚያን ዘመን አንድ ሰው ሁለት መቶ ቀናት ወይንም ሰባት ወራት ያህል ሰርቶ የሚያገኘው የገንዘብ መጠን ነው።

- የስምኦን ጴጥሮስ ወንደም እንድርያስ በሕዝቡ መካከል ምሳውን ይዞ የመጣ አንድ ልጅ መኖሩን ለኢየሱስ ነገረው። ልጁ ራሱ ወይንም ለልጁ የሚያስብ ሌላ አዋቂ ሰው ልጁ በዚህ ጉዞ እንዳይራብ በማሰብ አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ትንንሽ አሳዎችን አዘጋጀ። ምንም እንኳን ልጁ ይዞት የመጣው ምግብ ለራሱ ቢሆንም ኢየሱስ እንዲጠቀምበት ፈቀደለት።

- በዚያ ስፍራ ብዙ ለም ሳር ስለነበር ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ሕዝቡን 50 ወይንም 100 እያደረጉ ሕዝቡን በቡድን እንዲያስቀምጧቸው አዘዛቸው። ሰዉ ሁሉ ከተቀመጠ በኋላ ኢየሱስ እንጀራውን በእጁ ይዞ አመሰገነ። ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው። እንጀራው በተቆረሰ ቁጥር መባዛቱን ቀጠለ። እንጀራውን ደጋግመው ቆረሱት።

- በአሳውም ተመሳሳይ ነገር አደረገ። ደቀመዛሙርቱም ምግቡ ለሁሉም ሰው እስኪዳረስ ድረስ በሕዝቡ መካከል አካፈሉት። ሕዝቡ ከበሉ በኋላ ኢየሱስ ትርፍራፊውን እንዲሰበስቡ ደቀመዛሙርቱን አዘዛቸው። ምን ያህል እንደተረፈ መገመት ትችላላችሁ? አስራ ሁለት ሙሉ ቅርጫት እንጀራና አሳ!

- ከዚያም ኢየሱስ ይህን ሁሉ ሰው ሲመግብ ያዩ ሰዎች በሙሉ "እውነትም ይህ ወደአለም የሚመጣው እውነተኛው ነቢይ ነው።" ኢየሱስም በኃይል አስገድደው ሊያነግሱት እንዳሰቡ አውቆ ያንን ስፍራ ለቆ ወደሌላ ስፍራ ብቻውን ሄደ።

  *ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን በጥቂት እንጀራና አሳ እንደመገበ የሚናገረው ታሪክ በአዲስ ኪዳን በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6፡ 1 – 15 ውስጥ ይገኛል።*